የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ስድስተኛ ዓመት ቁጥር ፲፫
አዲስ አበባ የካቲት ፫ ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

26th Year No. 13
ADDIS ABABA 11th February, 2020

**<u>ማውጫ</u>**

ደንብ ቁጥር ፬፻፷፪/፪ሺ፲፪ ዓ.ም

የኢትዮጵያ የማዕድን፣ ነዳጅና ባዮፊዩል ኮርፖሬሽን እንደገና ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ……..ገጽ ፲፪ሺ፺፰

**<u>Content</u>**

Regulation No. 462/2020

Ethiopian Mineral, Petroleum and Bio-fuel Corporation Re-Establishment Council of Ministers Regulation………………...page 12098

ደንብ ቁጥር ፬፻፷፪/፪ሺ፲፪

## <u>የኢትዮጵያ የማዕድን፣ ነዳጅና ባዮፊዩል ኮርፖሬሽንን እንደገና ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ</u>

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት የአስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፺፯/፪ሺ፲፩ አንቀጽ ፴፬ እና በመንግሥት ልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ አንቀጽ ፵፯ (፩) (ሀ) እና (መ) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

**፩. <u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ ደንብ "የኢትዮጵያ የማዕድን ነዳጅና ባዮፊዩል ኮርፖሬሽን እንደገና ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፬፻፷፪/፪ሺ፲፪" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. <u>ትርጓሜ</u>**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ:-

፩/ "ማዕድን" ማለት ማናቸውም ዋጋ ያለው በጠጣር፣ በፈሳሽ ወይም በጋዝ መልክ በተፈጥሮ በመሬት ላይ ወይም ውስጥ፣ በውኃ ውስጥ ወይም ሥር የሚገኝ በሥነ-ምድር ሂደት ወይም ሁኔታዎች የተፈጠረ ሲሆን ቀደም ሲል ተቆፍሮ የወጣና ተርፎ በተቆለለ ማዕድን አዘል አፈር ወይም በቀሪ የማዕድን ክምችቶች ውስጥ የሚገኝ ማዕድንን ይጨምራል፤ ሆኖም የሚከተሉትን አይጨምርም:-

Regulation No. 462/2020

## <u>COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO RE-ESTABLISHMENT THE ETHIOPIAN MINERAL, PETROLEUM AND BIO-FUEL CORPORATION</u>

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 34 of the Definition of Power and Duties of the Executive Organs of the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia proclamation No. 1097/2018 and Article 47 (1) (a) and (d) of the Public Enterprises Proclamation No.25/1992.

**1. <u>Short Title</u>**

This Regulation may be cited as the "Ethiopian Mineral, Petroleum and Bio-fuel Corporation Re-Establishment Council of Ministers Regulation No. 462 /2020."

**2. <u>Definition</u>**

In this Regulation, unless the context otherwise requires:

1/ "Mineral" means any mineral substance of economic value, whether in solid, liquid or gaseous form, occurring naturally on or within the earth or in or under water and which was formed by or subjected to an ecological process, and include any mineral occurring in residue stockpiles or in residue deposits, but excludes:

ሀ) ለመታጠቢያ፣ ለመዝናኛ፣ ለሕክምና ከሚውሉ የጂኦተርማል ውኃና ከውስጡ ማዕድን ለማውጣት ከሚውል እንደ ብራይን ከመሳሰለ ውኃ በስተቀር ሌላውን ውኃ፤

ለ) አግባብ ባለው የነዳጅ ሕግ ትርጓሜ የሚካተቱ የተፈጥሮ ዘይትና ጋዝ፤

ሐ) ለም አፈርን እና ነዳጅ አዘል አለትን፤

፪/ “የማዕድን ሥራዎች” ማለት የማዕድናት ቅኝት፣ ምርመራ፣ ይዞ መቆየት፣ ወይም ማምረት ጋር የተያያዙ ተግባራት ሲሆኑ፤ የማናቸውም ማዕድናት ግብይት ሥራዎች መሥራትን ያካትታል፤

፫/ “ነዳጅ” ማለት ከኦይል ሼል ወይም ከታር ሳንድ የተገኘውን ኃይድሮካርቦን ጨምሮ የነዳጅ ድፍድፍ ዘይት እና የተፈጥሮ ጋዝ ሲሆን ከሼል ጋዝ፣ ከድንጋይ ከሰል እና ከባዮፊዩል ሥራዎች የሚመረቱ ተመሳሳይ ምርቶችን ያካትታል፤

፬/ “የነዳጅ ሥራዎች” ማለት ድፍድፍ ዘይትና የተፈጥሮ ጋዝ መፈለግ፣ ማልማት፣ ማውጣት፣ ማምረት፣ በመስክ መለያየት፣ ማዘጋጀት፣ ማከማቸት፣ ወደ ውጭ ሀገር እስከሚላክበት ወይም ለሀገር ውስጥ ፍጆታ ወደ ሚሰራጭበት ሥፍራ ማጓጓዝ እና የተጣሩ የነዳጅ ምርቶችን ለተጠቃሚ ማቅረብ ሲሆን፣ ከተፈጥሮ ጋዝ የተለያዩ ምርቶችን ማውጣትና የነዳጅ ድፍድፍ ዘይት ማጣራትን ይጨምራል፤

፭/ “ባዮፊዩል” ማለት በካርቦሃይድሬት እና በዘይት ከበለጸጉ የተክሎች ግንድ፣ ፍሬ፣ ሥር ወይም ቅጠል፤ የከተማ ውጋጅ፣ የግብርና እና የደን ተረፈ ምርት፣ አልጌ፣ ወይም የእንስሳት ስብ እና ጥቅም ላይ ከዋለ ዘይት በማቀነባበር የሚገኝ ታዳሽ የሆነ ፈሳሽ ነዳጅ ማለት ነው፤

፮/ “የባዮፊዩል ሥራዎች” ማለት ከሞላሰስ፣ ከተክሎች ከእንስሳት ስብና ከሌሎች የተለያዩ ግብዓቶች ባዩፊዩል የማምረት ተግባር ነው፤

፯/ “ሚኒስቴር” ወይም "ሚኒስትር" ማለት እንደ ቅደም ተከተላቸው የማዕድንና ነዳጅ ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፡፡

## ፫. <u>መቋቋም</u>

፩/ የኢትዮጵያ የማዕድን፣ ነዳጅና ባዮፊዩል ኮርፖሬሽን (ከዚህ በኋላ “ኮርፖሬሽን” እየተባለ የሚጠራው) የራሱ ህጋዊ ሰውነት ያለው የፌደራል መንግሥት የልማት ድርጅት ሆኖ በዚህ ደንብ እንደገና ተቋቁሟል፡፡

፪/ ኮርፖሬሽኑ በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ መሠረት ይተዳደራል፡፡

a) water, other than geothermal water that may be used for bathing, recreation and therapeutic purpose or water used for the extraction of any mineral such as brine;

b) natural gas and petroleum as defined in the relevant petroleum law;

c) top soil and oil shale;

2/ “Mining Operations” means any activity associated with or connected to reconnaissance, exploration, retention, or mining and includes engaging in transaction of any mineral;

3/ “Petroleum” means crude oil and natural gas and includes hydrocarbons produced from oil shale and tar sands; it shall also encompass similar products produced from shale gas, coal and bio-fuel operations;

4/ “Petroleum Operations” means the operation involving and related to the crude oil and natural gas exploration, development, extraction, production, field separation, treatment, storage, transportation up to the point of exportation or entry into a system for domestic consumption and marketing of petroleum products, including processing of natural gas and refining of crude oil;

5/ “Bio-fuel” means liquid renewable fuel derived from plant stems, seeds, roots or leaves, municipal waste, agriculture and forest residues, algae, or animal fat and waste vegetable oil which are rich in carbohydrate and oil;

6/ “Bio-fuel Operations” means activities related to the production of fuels from various feed stocks including molasses, plants and animal fats;

7/ “Ministry” or “Minister” means the Ministry or the Minister of Mines and Petroleum, respectively.

## 3. <u>Establishment</u>

1/ The Ethiopian Mineral, Petroleum and Bio-fuel Corporation (hereinafter referred to as the “Corporation”) having its own legal personality is hereby established as a Federal Government Public Enterprise.

2/ The Corporation shall be governed by Public Enterprises Proclamation No.25/1992.

**፬. ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን**

ሚኒስቴሩ የኮርፖሬሽኑ ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ይሆናል፡፡

**፭. ዋና መሥሪያ ቤት**

የኮርፖሬሽኑ ዋና መሥሪያ ቤት አዲስ አበባ ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ በሌሎች ስፍራዎች ቅርንጫፍ ሊኖረው ይችላል፡፡

**፮. ዓላማ**

ኮርፖሬሽኑ የተቋቋመበት ዓላማ የሚከተሉት ናቸው:-

፩/ በማዕድን፤ በነዳጅና በባዮፊዩል ሥራዎች ውስጥ በቀጥታ በመሳተፍ የሀገራችን የተፈጥሮ ሃብት በተገቢ ሁኔታ በማልማት የበለጠ ተጠቃሚ እንድትሆን ማስቻል፤

፪/ ሀገር በቀል አቅምን በመገንባትና በዘርፉ ለተሰማሩ ባለሃብቶች እገዛ በማድረግ የሀገራችንን ተጠቃሚነት ማረጋገጥ፤

፫/ ከስትራቴጂካዊ አስፈላጊነታቸው አንፃር ከፍተኛ ግምት በሚሰጣቸውና በግሉ ዘርፍ ሊሟሉ በማይችሉ ዘርፎች ላይ በመሳተፍ ክፍተቱን መሙላት፤

፬/ በዘርፉ ተወዳዳሪ የመንግሥት ልማት ድርጅት በመሆን ለሀገራችን ኢኮኖሚ ግንባታ እገዛ ማድረግ እንዲሁም

፭/ ዓላማውን ለማሳካት የሚያስችሉ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

**፯. ካፒታል**

ለኮርፖሬሽኑ የተፈቀደ ካፒታል ብር ፲፮ ቢሊዮን ፯፻ ሚሊዮን (አሥራ ስድስት ቢሊዮን ሰባት መቶ ሚሊዮን) ሲሆን ከዚህ ውስጥ የተከፈለው ካፒታል ብር ፬ ቢሊዮን ፩፻፸፭ ሚሊዮን (አራት ቢሊዮን አንድመቶ ሰባ አምስት ሚሊዮን) በጥሬ ገንዘብና በዓይነት ተከፍሏል፡፡

**፰. ኃላፊነት**

ኮርፖሬሽኑ ካለው ጠቅላላ ንብረት በላይ በዕዳ ተጠያቂ አይሆንም፡፡

**፱. ኮርፖሬሽኑ የሚቆይበት ጊዜ**

ኮርፖሬሽኑ ላልተወሰነ ጊዜ ይቆያል፡፡

**፲. የተሻሩ ደንቦች**

የኢትዮጵያ የማዕድን፣ ነዳጅና ባዮፊዩል ኮርፖሬሽን ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፫፻፷፯/፪ሺ፯ (እንደተሻሻለ) በዚህ ደንብ ተሽሯል፡፡

**4. Supervising Authority**

The Ministry shall be the Supervising Authority of the Corporation.

**5. Head Office**

The Corporation shall have its Head Office in Addis Ababa and may have branch offices elsewhere as may be necessary.

**6. Purpose**

The purpose for which the Corporation is established are:

1/ to ensure that the country benefits from its natural resources by developing and directly engaging itself in the mining, petroleum and bio-fuel sectors;

2/ to ensure the country benefits from the sector by building local capacity and supporting investors engaged in the sector;

3/ to fill the gaps by engaging in sectors which have strategic importance but cannot be addressed by the private sector;

4/ to contribute to the national economy by being competent public enterprise in the sector, and

5/ undertake other activities which are essential for the achievement of its objectives.

**7. Capital**

The authorized capital of the Corporation is Birr 16,700,000,000 (Sixteen Billion Seven Hundred Million) out of which Birr 4,175,000,000 (Four Billion One Hundred Seventy Five Million) is paid up in cash and in kind.

**8. Liability**

The Corporation shall not be held liable beyond its total assets.

**9. Duration of the Corporation**

The Corporation is established for unlimited period.

**10. Repealed Regulations**

The Ethiopian Mineral, Petroleum and Bio-fuel Corporation Establishment Council of Ministers Regulation No. 367/2015 (as amended) is hereby repealed.

**፲፩. <u>መብቶችና ግዴታዎች መተላለፍ</u>**

የሚከተሉት የመንግሥት ልማት ድርጅቶች መብቶችና ግዴታዎች በዚህ ደንብ ለኮርፖሬሽኑ ተላልፈዋል:-

፩/ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፫፻፷፯/፪ሺ፯ (እንደተሻሻለ) ተቋቁሞ የነበረው የኢትዮጵያ ማዕድን፣ ነዳጅና ባዮፊዩል ኮርፖሬሽን፤

፪/ የአዶላ ወርቅ ልማት ድርጅት፤

**፲፪. <u>ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ</u>**

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ የካቲት ፫ ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ.ም

**ዶ/ር አብይ አህመድ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**

**ጠቅላይ ሚኒስትር**

**11. <u>Transfer of Rights and Liabilities</u>**

The rights and liabilities of the following public enterprises are hereby transferred to the Corporation:

1/ The Ethiopian Mineral, Petroleum and Bio-Fuel Corporation which was established under the Council of Ministers Regulation No. 367/2015 (as amended);

2/ Adola Gold Mining Enterprise.

**12. <u>Effective date</u>**

This Regulation shall enter into force on the date of its publication in the Federal Negarit Gazette.

Done at Addis Ababa this 11th day of Februrary /2020.

**ABIY AHMED (DR.)**

**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**